የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ		
I. አጠቃላይ መግለጫ		
የመሥሪያ ቤቱ ስም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት
ጤና ጥበቃ ሚ/ር	የፊዚዮቴራፒ ህኪም III	ፊዚዮቴራፒ
የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ /ተጠሪነት	በሲቪል ሰርቪስ ሚኒስቴር/ቢሮ ብቻ የሚሞላ	
	የሥራው ደረጃ	የሥራው ኮድ
	XVI	ፊዚዮቴራፒ
መሥሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ		
በየደረጃው ባሉ ሆስፒታሎች		
II. የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ ውጤቶችና ተግባራት		

2.1. የሥራ መደቡ ዓላማ፡-

- የፊዚዮቴራፒ ህክምና፣ የጤና ማበልፀግና በሽታ የመከላከል ትምህርት፣ የተሃድሶ አገልግሎት በመስጠትና በፊዚዮቴራፒ ህክምና ዙሪያ ምርምርና ጥናት በማካሄድ፣ እንዲሁም ምክርና የአቅም ግንባታ በመስጠት የታካሚውን ጤንነት መመለስ፣ ማህበረሰቡን ተላላፊና ተላላፊ ካልሆኑ በሽታዎች መከላከልና አካል ጉዳተኞችን በማብቃት ወደ ምርታማነት በመመለስ፣ የሃገሪቱን የአካል ጉዳተኝነት መከሰትን መቀነስና የህብረተሰቡን ጤና እንዲጠበቅ ማድረግ ነው።

2.2.የሥራ መደቡ ውጤቶችና ተግባራት

ውጤት **1**፡ የፊዚዮቴራፒ ህክምና መስጠት

- ማንኛውንም የፊዚዮቴራፒ ህክምና ተገልጋይ እንደ እምነቱና ባህሉ መሠረት ተገቢውን ርህራሄ፤ አክብሮትና ጥንቃቄ በማድረግ በተሟላ ሁኔታ ያስተናግዳል፤
- በድንገተኛ ህክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ታካሚዎች ቅድመ ልይታና መረጣ (triage) በማድረግ፣ የህይወት መቀጠል (ABC of life, Basic and Advanced life support) ምርመራና ህክምና ዕርዳታ ይሰጣል።
- የፊዚዮቴራፒ ህክምና የሚያስፈልገዉን ታካሚዉ የህክምና ታሪክ ይወስዳል፣ የታካሚዉን የህክምና መረጃ ያያል፣ አስፈላጊዉን አካላዊ ምርመራ ያደርጋል፣ ዲያግኖስቲክ ምርመራ(ለምሳሌ ራጅ፣ሲቲስካን፣ ኤም አርአይ...ወዘተ) እና የላቦራቶሪ ምርመራዎች እንዳስፈላጊነቱ ያዛል። በዉጤቱ ላይ በመመርኮዝ በሽታውን ይለያል፣ የበሽታውን ዕጣ ፈንታ (prognosis) ሳይንሳዊ ግምት ይሰጣል፣ የሉትን የህክምና አማራጮች ለታካሚው እንዳስፈላጊነቱ ለቤተ-ሰቡ ያስረዳል።
- **አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የመድሀኒት አለርጂ በመተንተንና አለመኖሩን በማረጋገጥ** ተስማሚ መድሃኒቶችን ያዛል፣ በተጨማሪም በጅማት፣በጡንቻና በመገጣጠሚያ በመርፌ መድሃኒት ይሰጣል።

- መስመራቸውን ያልሳቱ ስብራቶች እና ቀላል የመገጣጠሚያ ዉልቃቶችን ያስተካክላል፣ ጀሶና ሌሎች የእንቅስቃሴ ማገጃዎችን (Braces) በመጠቀም ያክማል፣ አስፈላጊ ምርመራዎችን በማዘዝ የእንቅስቃሴ ማገጃዎቹ የሚፈቱበትን ጊዜ ይወስናል፣
- በውድድርም ሆነ በልምምድ ጊዜ በስፖርት ላይ የሚደርሱ አደጋና ጉዳቶችን ከህክምና ተቋማት በተጨማሪ እንዳስፈላጊነቱ ስፖርቱ የሚከናወንበት ቦታ በመገኘት ያክማል።
- የነርቭ ማስተላለፍ ብቃት መለካት (nerve conductin study) ምርመራና የጡንቻ የኤሌክትሪካዊ መለኪያ(EMG) በመጠቀምም ምርመራ ያደርጋል፤ ያክማል።
- በልብ፣ በደም ዝዉውርና በመተንፈሻ አካላት የጤና እክሎች(Cardiac, circulation and pulmonary conditions) እንዳስፈላጊነቱ የአካል ብቃት፣ የአተነፋፈስና የልብ ብቃትና የልብ ጫና (physical fitness, aerobic capacity endurance test, cardiopulmonary fitness, cardiac stress test,) እና የልብን ኤሌክትሪካዊ ብቃት (ECG) ምርመራ ያደርጋል፣ በውጤቱም በመመርኮዝ አስፈላጊዉን የፊዚዮቴራፒ ህክምና ይሰጣል።
- የልብ አመታትና የመተንፈሻ አካላትን ብቃት በሚለኩ መሳርያዎችና ዘዴዎች በመታገዝ የህሙማኑን የማገገም ደረጃ ይቆጣጠራል፣ የልብ አመታትና የመተንፈሻ አካላትን ብቃት የሚያሻሽሉ ስልቶችና ኮምፕሌክስ ዲኮንጀስቲቭ ህክምና ይሰጣል፣ ውጤቱንም የተለያዩ የህክምና መሳርያዎች በመታገዝ ይቆጣጠራል።
- የደም ዝውውር እክሎች(Peripheral arterial disease) እንዳሉ ሲጠረጠር ዶፕለር ልዕለ ድምፅ (Dopplar ultra sound) ምርመራ በማድረግ የደም ዝውውሩን ይመረምራል፣ አስፈላጊዉን የፊዚዮቴራፒ ህክምና ይሰጣል፣ እነዚህንም ውጤቶች ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች፣ ህመምተኛው እና የህመምተኛው ቤተሰቦች ጋር ይመካከራል ።
- እንደ ታይቺ፣ ፒላቴ፣ ፊልደንክራስና አሌክዛንደር ያሉ በአትኩሮት የሚሰሩ አካላዊእንቅስቃሴዎችንና ሌሎች ሙያዊ ስለቶችን በመጠቀም ፐርሴፕቹዋል ህክምና (perceptual training)፣ የአቋም ግንዛቤና ሴንሰሪ ትሬኒንግ ህክምና (sensory training or retraining) ይሰጣል።
- ሚዛን የመጠበቅ እና የአንጎል፣ የጡንቻና የመገጣጠሚያ መስተጋብር ህክምና (Balance and coordination), ጌትና ሎኮሞተሪ ህክምና (gait and locomotor training) የጉልበት ብክነት መከላከል ህክምና (movement efficiency and energy conservation training), ኒዉሮ መስኩላር ኤጁኬሽን (Neuromuscular education or re-education) ህክምና ይሰጣል።
- ታስክ ስፔስፊክ ፐርፎርማንስ ህክምና (task-specific performance training)፣ ቬስቲቡላር ህክምና (vestibular training)፣ የዕለት ተዕለት መሰረታዊ የህይወት እንቅስቃሴ ህክምና (Activities of daily life training) ፣ ፕሮፕሮሴፕቲቭ ህክምና (Proprioceptive training)ይሰጣል።
- ቁስሎችን መርምሮ በመስፋት፣ ዲብሪድ በማድረግ (debridment)፣ ቁስሎችን በፍጥነት ለማዳን የሚያግዙ የተለያዩ የፊዚዮቴራፒ ህክምና መሳሪያዎችንና ሌሎች ሙያዊ ስልቶችን በመጠቀም ያክማል እንዲሁም ኢንፌክሽን እንዳይከሰት ከሚመለከታቸው የህክምና ባለሙያዎች ጋር ሆነው ይማከራል፤ ይሰራል።
- ከካንሰር በሽታና ከህክምናው (ጨረር፣ ኬሞቴራፒና ሰርጀሪ) ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ከፍተኛ ህመሞችንና የጎንዮሽ ጉዳቶችን

ለምሳሌ ከፍተኛ አካላዊ ዝለት(fatigue)፣ የጡንቻ መመንመን(cancer cachexia)፣ ተፈጥሯዊ የበሽታ መከላከል አቅም ድክመት ... ወዘተ የተለያዩ ሙያዊ ዘዴዎች በመጠቀም ያከማል። መዳን ለማይችሉ ታማሚዎች የፓሌቲቭ ኬር ህክምና መስጠት ላይ ይሳተፋል።

- በዳሌ ንጣፍ ጡንቻዎች ድክመት ምክንያት ሽንትን ለመቆጣጠር በሚያዳግታቸው ህሙማን ላይ፤ የፊዚዮቴራፒ ህክምና መሳርያዎችን በመጠቀም የነርቭና የጡንቻ ማነቃቂያ ህክምና ይሰጣል፣ተያያዥነት ያላቸውን የሰውነት አካላት በማነቃቃት እንዲጠነክሩ የሰውነት እንቅስቃሴ ህክምና ያዛል፣ያስተምራል፣ ከሚመለከታቸው ባለሙያዎች፣ከህመምተኛው እና የህመምተኛው ቤተሰቦች ጋር ይመካከራል።
- በእድሜ ምክንያት የሚመጡ ህመሞች እና አካላዊ ችግሮች (Geriatric conditions) አዛውንቶች እራሳቸውን ችለው የእለት ከእለት ኑሮአቸውን እንዳይገፉ የሚከለክሉ ስጋት በመለየት የመፍትሄ ህክምና ይሰጣል፤ በሽታዎቹም ወይም አካላዊ ችግሮቹም ሲከሰቱ ያክማል።
- የነርቭና የጡንቻ ማነቃቂያ ህክምና፣ ዲፕ ቴንደን እና የጡንቻ ፋሲሊቴሽን እና ኢንሂቢሽን፣ ኮንስትሪየንት እንዲዩስድ ህክምና (constraint induced therapy) እንዲሁም ተያያዥነት ያላቸውን ህክምና ይሰጣል።
- የኮር (Core stabilizers) እና የተለያዩ የሰውነት ጡንቻ ማነቃቂያ፣ የማሳሳቢያ፣ የማፍታቻ፣ ማጠንከርያ እና የደም ዝዉውር ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎችን (Stimulation, stretching, relaxation, strengthening, power, agility, endurance and blood circulation facilitation exercises) ያዛል፣ በመጠቀም ያክማል፣ ይቆጣጠራል።
- የቴራፒውቲክ አልትራሳውንድ፣ የሌዘር ጨረር(Laser)፤ ሜካኒካል ዲኮምፕሬሰር፣ ራዲዮ ሾክ ዌቭ፣ አዮንቶ ፎሬሲስ ፣ ክራዮ ፓምፕ እና የመሳሰሉትን የህክምና መሳርያዎችን በመጠቀም የነርቭና የጡንቻ ማነቃቂያ፣ የህመም ማስታገሻና ማጥፊያ ህክምና ይሰጣል።
- የመጋጠሚያና የአከርካሪ አጥንት ማኑፑሌሽን ሞቢላይዜሽን (high velocity low amplitude mobilization and trust)፣ የጡንቻና ፋሻ ሞቢላይዜሽን እና የነርቭ ግላይድ (Nerve glide) ህክምና ይሰጣል።
- የደረቅ መርፌ ህክምናን (Dry needling) ጨምሮ የሚያስፈልጉ የፊዚዮቴራፒ ህክምና ስልቶችን በመጠቀም የእያንዳንዱን ታካሚ የጤና ዕክል ለመቅረፍ የሚያስፈልግ ግላዊ (Individualized) ህክምና ይሰጣል።
- ከአቅም በላይ የሆኑ ወይንም የሌላ ባለሞያ አስተያየትና ምክር የሚፈልጉ የህክምና ችግሮችን በመለየት ወደ የሚመለከተው የህክምና ባለሙያ (ስፔሻሊስትና ሱፐር ስፔሻሊስት) ወይም ተቋም በወቅቱ ይልካል።
- በህክምናዉ ሂደት ላይ ያለዉን ለታካሚዉ የተሠጡ አገልግሎቶችና ውጤት በታካሚው ካርድ ላይ ይመዘግባል፣ ሚስጥር ይጠብቃል፣ አስፈላጊ ድጋፍ፣ ክትትል እና ቀጠሮ ይሰጣል። የታካሚዉን ዉጤት በማሳወቅ ዉሳኔ ይሰጣል፣ ህክምናቸዉን የጨረሱ ታካሚዎችን ሙያዉ በሚጠይቀዉ መስፈርት መሰረት ከህክምና ተቋሙ ሰናብታል(discharge)፣ የህመም ፍቃድና የህክምና ማስረጃ(ሰረተፍኬት) ይሰጣል።

- የፊዚዮቴራፒ ህክምና አገልግሎቱን ጥራት በተዘጋጁ መስፈርቶች መሰረት መሰጠታቸውን ያረጋግጣል፣
- የክፍሉን የስራ ዕቅድና ክንውን ሪፖርት ያቀርባል፣

ውጤት 2፡ ጤና ማበልፀግና በሽታ መከላከል ህክምና መስጠትና ማማከር

- የሰዉነት አቋምን (postural alignment & Ergonomics) ይመረምራል፣ ካልተስተካከለ አቋም የተነሳ ሊመጡ የሚችሉ የጤና ስጋቶችን ቀድሞ በመለየት የማስተካከያ ህክምና ይሰጣል፣ መከላከሉ ሳይሳካ ቀርቶ ችግሮችም ከተከሰቱ ያክማል።
- ስለጤናማ አኗኗር ዘይቤ (Healthy life style) ፣ ያማክራል፣ ትምህርት ይሰጣል። ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች እንዲሁም ከእንቅስቃሴ ማነስ ጋር ተያይ የሚከሰቱ በሽታዎችን እንዳይከሰቱ የግንዛቤ ትምህርት እና የመከላከል ህክምና ይሰጣል።
- ከአደጋ፣ ጉዳትና ቀዶ ጥገና በኋላ የሚከሰቱ የመገጣጠሚያ አለመንቀሳቀስ፣ የሰዉነት አለመታዘዝና የጠበሳ(Scar) እንቅስቃሴ መገደብ እንዳይከሰት ይመረምራል፣ ያክማል።
- በስፖርት ላይ የሚደርሱ አደጋና ጉዳቶች የመከላከል ስልጠናና የቅድመ ጥንቃቄ ህክምና ይሰጣል፣ የጥንቃቄ መሳሪያዎችን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመነጋገር ስፖርተኞቹ እንዲጠቀሙ ያደርጋል።
- በደም ስሮች ውስጥ የደም መርጋት (Deep venous thrombosis) ለመከላከል የሚረዳ ህክምናና የግንዛቤ ምክር ይሰጣል።
- በእድሜ ምክንያት የሚመጡ ህመሞች እና አካላዊ ችግሮች (Geriatric conditions) አዛውንቶች እራሳቸውን ችለው የእለት ከእለት ኑሮአቸውን እንዳይገፉ የሚከለክሉ ስጋት በመለየት የመፍትሄ ህክምና ይሰጣል።
- የመውደቅ አደጋ ተጋላጭነትን STEADI እና ሌሎች የመለያ መሳሪያዎችን በመጠቀም ለይቶ አስፈላጊውን የመከላከያ ህክምናና የጥንቃቄ ምክር ይሰጣል።
- በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰቱ የሚችሉ የእንቅስቃሴ ችግሮችንና በሽታዎችን ቀድሞ በመለየት ይከላከላል፣ ያክማል፣ ስለ ስጋቶቹም ያስተምራል።
- በህመም ምክንያት ረጅም ጊዜ የሚተኙ ታካሚዎችና የተንቀሳቃሽ ወንበር (wheelchair) ተጠቃሚዎች ስለ pressure ulcer መከላከል ትምህርትና ህክምና ይሰጣል።
- ብዙሃን ላይ ድንገተኛ አደጋ (mass casuality) በሚከሰትበት ጊዜ የምርመራና የህክምና አገልግሎት መስጠት ላይ ይሳተፋል። በድንገተኛ አደጋ ጊዜ እርዳታ ሰጪዎች ጉዳቱ እንዳይባባስ መድረግ ስላለባቸው ጥንቃቄዎች ስልጠናና የግንዛቤ ምክር ይሰጣል።

ዉጤት **3**፡ የተሃድሶ አገልግሎት መስጠት እና የአቅም ግንባታ ሥራ መስራት

- አካል ጉዳት መከላከልንና ከተከሰተ በኋላ የሚያደርሰዉን ተጽዕኖ ተቋቁሞ መኖርን በተመለከተ ለታካሚዉና ለቤተሰቦቹ የግንዛቤ መረጃ ይሰጣል።

- አካል ጉዳት የደረሰባቸው ታካሚዎች ማህበራዊና ስነልቦናዊ ጥንካሬና ብርታት እንዲያገኙ፣ ጤናማ ህይወት እንዲመሩ የምክር

አገልግሎት ይሰጣል።

- አካል ጉዳት ለደረሰባቸውን ታካሚዎች የዕለት ተዕለት ኑሮ እንቅስቃሴአቸውን ለማሻሻል እና ለማንለብት እንዲሁም ከጥገኝነት ለማላቀቅ ስልቶችን ይቀይሳል፤ የክህሎት መልመጃ ና ማዳበሪያ ግንባታ ይሰጣል።
- አስፈላጊዉን ሰው ሰራሽ አካል ፣የአካል ድጋፍና ደጋፊ የመንቀሳቀሻ መሳሪያዎች ለምሳሌ ክራንች፣ዊል ቸር፣አመቺ የሆኑ ጫማዎችን ... በታካሚው መጠንና የድጋፍ አስፈላጊነት ልክ ለይቶና ለክቶ እንዲዘጋጁ ያዛል፤ ስለ አጠቃቀማቸውም ልምምድና ስልጠና ይሰጣል።
- በስፖርት ላይ ከፍተና አደጋና ጉዳቶች ሲከሰቱ የተሃድሶ ህክምና ይሰጣል።
- በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና ይሰጣል፤
- በአካል ጉዳተኛ ዙሪያ ከሚሰሩ ማህበራትና ድርጅቶች ጋር በትብብር ይሰራል፣ የተሃድሶ ህክምናንና በተመለከተ ያማክራል ።
- በህክምና ተቋማትና በተሃድሶ ማዕከላት በሚሰጡ የተሃድሶ አገልግሎት ዙሪያ ያማክራል፣ አገልግሎቱንም ይመራል : :
- ከማህበረሰብ አቀፍ ተሃድሶ ባለሙያዎች ጋር በቅንጅት ይሰራል፣ ስለ አገልግሎቱም ያማክራል፣ የአቅም ግንባታ ይሰጣል።

ዉጤት 4፡- በፊዚዮቴራፒ ህክምና ዙሪያ የሥልጠና ክፍተት መለየት ትምህርትና ስልጠና መስጠትና ጥናትና ምርምር ማካሄድ

- በፊዚዮቴራፒ ህክምና፣ በተሃድሶ አገልግሎትእና ሌሎች የጤና ዘርፍ ዙሪያ ዙሪያ **የምርምር ፕሮፖዛሎችና መረጃ ማሰባሰቢያ ቅፆች ያዘጋጃል፣ ሙያው ለሚመለከታቸው ሰዎች (በህብረተሰብ ጤና ስፔሻሊስቶች እና ስታቲሰቲክስ ባለሙያዎች) መረጃዎችን ያስገመግማል፣ እንዲፀድቁለት ያደርጋል።**
- **የዕውቀትና የክህሎት ክፍተት በመለየት ለጀማሪዎችና ለሚመለከታቸው አካላት የተለያዩ የአጫጭር ስልጠናዎችን በማዘጋጀት ይሰጣል።**
- የፊዚዮቴራፒ ህክምናና የተሃድሶ ህክምና **መረጃዎችን ይሰበስባል፣ ወደ ኮምፒውተር በማስገባት ይተነትናል**
- **የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የባለሙያዎችን የእውቀትን ክህሎት ክፍተት ይለያል፤**
- በፊዚዮቴራፒ ህክምና ዙሪያ **ለተለዩ ክፍተቶች የስልጠና ማኑዋል እንዲዘጋጅ ያድርጋል፤**
- የፊዚዮቴራፒ ህክምናና የተሃድሶ ህክምና በተመለከተ ከሙያው **ለተግባር ልምምድ ወደ ተቋሙ የመጡትን ባለሙያዎች ያሰለጥናል**
- የፊዚዮቴራፒ ህክምናና የተሃድሶ ህክምና ዘርፍ የሥልጠና ክፍተት ያለባቸውን ለማወቅ የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፤
- የፊዚዮቴራፒ ህክምናና የተሃድሶ ህክምና በዘርፉ ለተሰማሩ አካላት ሥልጠና ለመስጠት የሚያስችሉ የሥልጠና ሰነዶችን ያዘጋጃል፤
- ሥልጠና ለመስጠት ከተለያዩ አካላት ፕሮጀክት በመቅረፅ ገቢ ያፈላልጋል
- የተሰጠው ስልጠና ያመጠውን ፋይዳ ለማወቅ የሚያስችል ጥናት ያካሂዳል፤

III. የሥራው ባህርይ መግለጫዎች

3.1. የሥራ ውስብስብነት

- ሥራው በድንገተኛ ህክምና እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ታካሚዎች ቅድመ ልይታና መረጣ (triage) ማድረግ፣ ፣ የፊዚዮቴራፒ ህክምና ያሚያስፍልጋቸውን ታካሚዎች ማከም፣ ስብራቶች እና ቀላል የመገጣጠሚያ ዉልቃቶችን ማከም፣ በስፖርት ላይ የሚደርሱ አደጋና ጉዳቶችን ማከም፣ የነርቭ ማስተላለፍ ብቃትና የጡንቻና የልብ የኤሌክትሪካዊ መለኪያ፣ በመጠቀም ምርመራ ማድረግ፣ ውጤቱን በመረዳት የችግሩን ደረጃ ማወቅ፣ በልብ፣ በደም ዝዉውርና በመተንፈሻ አካላት የጤና እክሎችን ምርመራ ማድረግ፣ አስፈላጊ መሳርያዎችና ዘዴዎች በመታገዝ የህሙማኑን የማገገም ደረጃ መቆጣጠርና ብቃትውን የሚያሻሽሉ ስልቶች በመጠቀም ህክምና መስጠት፣ ውጤቱንም መቆጣጠር፣ የደም ዝውውር እክሎች በዶፕለር መመርመርና፣ አስፈላጊዉን የፊዚዮቴራፒ ህክምና መስጠት፣ እንዲሁም ፐርሴፕቸዋል ህክምና ፣ የአቋም ግንዛቤና ሴንሰሪ ትሬኒንግ ህክምና ፣ሚዛን የመጠበቅና የአንጎል፣ የጡንቻና የመገጣጠሚያ መስተጋብር ህክምና ፣ ጌትና ሎኮሞተሪ ህክምና ፣የጉልበት ብክነት መከላከል ፣ ኒዉሮ መስኩላር ኤጁኬሽን ህክምና ፣ ታስክ ስፔስፊክ ፐርፎርማንስ ህክምና፣ ቬስቲቡላር ህክምና፣ የዕለት ተዕለት መሰረታዊ የህይወት እንቅስቃሴ ህክምና፣ ፕሮፕሮሴፕቲቭ ህክምና መስጠት፤ ቁስሎችን መርምረው በመስፋት፣ ዲብሪድ በማድረግ ማከም፣ ኢንፌክሽን እንዳይከሰት ማማከር፣ የካንሰር በሽታና ከህክምናው ጋር ተያይዞ የሚከሰቱ ከፍተኛ ህመሞችንና የጎንዮሽ ጉዳቶችን ማከም፣ ፓሌቲቭ ኬር መስጠት፣ ሽንት የመቆጣጠር ችግር ማከም፣ ከበእድሜ ምክንያት የሚመጡ ህመሞች እና አካላዊ ችግሮች ህክምና መስጠት፤ የነርቭና የጡንቻ ማነቃቂያ ህክምና፣ ዲፕ ቴንደን እና የጡንቻ ፋሲሊቴሽን እና ኢንሂቢሽን፣ ኮንስትሪየንት እንዲዩስድ ህክምና፣ የኮር እና የተለያዩ የሰውነት ጡንቻ ማነቃቂያ፣ የማሳሳቢያ፣ የማፍታቻ፣ ማጠንከርያ እና የደም ዝዉውር ማጎልበቻ እንቅስቃሴዎችን በመጠቀም ማከም፣ የቴራፒውቲክ አልትራሳውንድ፣ የሌዘር ጨረር፤ ሜካኒካል ዲኮምፕሬሰር፣ ኢንፍራሬድ፣ ራዲዮ ሾክ ዌቭ፣ አየንቶ ፎሬሲስ ፣ ክራዮ ፓምፕ እና የመሳሰሉትን የህክምና መሳርያዎችን በመጠቀም ህክምና መስጠት፣ የመጋጠሚያና የአከርካሪ አጥንት ማኑፑሌሽን ሞቢላይዜሽን፣ የጡንቻና ፋሻ ሞቢላይዜሽን እና የነርቭ ግላይድ፣ የደረቅ መርፌ ህክምና መስጠትና ከአቅም በላይ የሆኑ ወይንም የሌላ ባለሞያ አስተያየትና ምክር ለሚፈልጉ የህክምና ችግሮች በመለየት ወደ የሚመለከተው የህክምና ባለሞያ ወይም ተቋም መላክ፤ የተሠጡ አገልግሎቶችና ውጤት በታካሚው ካርድ ላይ መመዝገብ፣ ሚስጥር መጠበቅ፣ ድጋፍ፣ ክትትል እና ቀጠሮ መስጠት፣ የታካሚዉን ዉጤት በማሳወቅ ዉሳኔ መስጠት፣ ህክምናቸዉን የጨረሱ ታካሚዎችን ከህክምና ተቋሙ ማሰናበት፣ የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አስፈላጊዉን ሰውሰራሽ አካል፣የአካል ድጋፍና ደጋፊ የመንቀሳቀሻ መሳሪያዎች እንዲዘጋጁ ማዘዝ፣ ስለአጠቃቀማቸውም ማሰልጠን፣ የክፍሉን የስራ ዕቅድና ክንውን ሪፖርት **በማዘጋጀት ማቅረብ፤ በተቋሙ ውስጥ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎችን የመከላከልና የመቆጣጠር ስራን መስራት፣ ህሙማንን በተመለከተ በህኪሞች ውይይት ላይ መሳተፍ፤ ለምርምር ፕሮፖዛሎችና መረጃ ማሰባሰቢያ ቅፆች ዝግጅት ማዘጋጀት፣ ማስገምገም፣ ማጸደቅ፤ መረጃዎችን በመተንተን ችግሮችን መለየትና የመፍትሄ ሃሳቦችን ማቅረብ፤ የዳሰሳ ጥናት በማድረግ የባለሙያዎችን የእውቀትን ክህሎት ክፍተት መለየት፤ የፊዚዮቴራፒና የተሃድሶ** ሕክምና የስራ፣ የትምህርትና ስልጠና መርጃዎች ማዘጋጀት፣ ትምህርትና ስልጠና መስጠት፤ ስልጠናዉ ያመጣውን ፋይዳ በጥናት መለየት፣የስልጠናዉ ፍልጎትን በጥናት መለየት ሲሆን
- ስራው በሚከናወንበት ወቅት ፍጥነትና ጥንቃቄ የሚያስፈልግ መሆን፣ ከበሽታዎችና ችግሮች መብዛት የተነሳ ለመለየት አዳጋች

መሆን፤ **የበሽታዎች የተለዋዋጭነት ባህሪ ፈታኝ መሆን፤ የተለያዩ ህመሞች ተመሳሳይ ምልክቶች መያዛቸው፤ አንዳንድ በሽታዎችን በህክምና መመርመሪያ መሳሪያዎች በአርግጠኝነት ለመለየት አስቸጋሪ መሆናቸው፤ የተለያየ ጥንካሬና ውጤት ያላቸው መድሀኒቶች መኖራቸውና ለይቶ ለማዘዝ ክባድ መሆናቸው፤ ለአንዳንድ በሽታዎች የምርመራ ዘዴም ሆነ ሙሉ ለሙሉ የሚያድኑ መድሀኒቶች አለመገኘታቸው፣ የማህበረሰቡ በህክምና ላይ ያለው ግንዛቤ ውስን መሆን፣** የእያንዳንዱ ታካሚ በሽታ በተጨማሪ ሌሎች ተያያዥ ችግሮችን መኖር፣ **ህክምና በኋላ የሚከሰቱ የጎንዮሽ ችግሮችንና አለርጂዎችን አስቀድሞ መተንበይና ማስቀረት አለመቻል፣ ከተከሰቱ በኋላ ተገቢ የሆኑትን የማስተካከያ ህክምናዎችን ለመስጠት ጥናትና ምርምር አለማግኘት፣** በህመምተኛ የህክምናውን ባለመቀበል ለተጨማሪ በሽታ መጋለጥና ችግሩ እንዲባባስ ማድረግ፣ በእያንዳንዱ ቀን ህክምናዉ ረዥም ጊዜ መውሰድ እንዲሁም አንድ ታካሚ ረዥም ጊዜ ክትትል ማስፈለጉ፣ የታካሚዎች ዉጤት በሚጠበቀው ጊዜ ያለመሻሻል፣ ከሌሎች የህክምና ባለሙያዎች እና የህክምና ክፍሎች ታካሚዎችን በትክክል አለመላክ (refer አለማድረግ)ና ዘግይቶ መላክ፣ አስፈላጊዉን ሰው ሰራሽ አካል ፣የአካል ድጋፍና ደጋፊ የመንቀሳቀሻ መሳሪያዎች በታዘዝበት ጊዜና በሚያገኝበት ጊዜ የታካሚዉ ብቃት መለወጥ፣ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰቱ የሚችሉ የእንቅስቃሴ ችግሮችንና የሽታዎችን ስጋት ቀድሞ ለማወቅ አዳጋች ሞሆን፣ ለታካሚ የዕለት ተዕለት ኑሮ እንቅስቃሴ፣ ክህሎት ስልጠናና ህክምና ለመስጠት ከታካሚዉ ግንዛቤ አለመኖርና የታካሚዎች ወይም የቤተ_ሰባቸው አለመተባበር፣ በተሃድሶ ህክምና ላይ የግንዛቤ እጥረት መኖር፣ የተዘጋጁ የስልጠና ሰነድ አለመኖር፣ የሰለጣኞች የስልጠና ፍላጎት ተለይቶ አለመቅረብ፣ የተደራጀ መረጃ አለመግኘት፣ መስጠት፤መረጃዎቹ በተሞላ ሁኔታ ተሰብስቦ አለመገኘት እና ሰልጣኞች ስልጠናዉን አለመረዳት ፤ስልጠናዉ ያመጣውን ፋይዳና ፍልጎትን በጥናት መለየት አለመቻል የሚያጋጥሙ ችግሮች ሲሆኑ

- ችግሮቹንም ለመፍታት የባለሙያዉን የመመርመርና የማከም ክህሎትና ዕውቀት ማሻሻልና በመረጃ የተደገፈ (evidence based practice) ህክምና በመስጠት፣ ለሁሉም ታካሚ አስፈላጊውን ጥልቅ **የሆነ ቃለመጠይቅና የአካል** ምርመራ ማድረግ፣ ፤ **አስፈላጊ የሆኑ የላብራቶሪና የድያግኖስቲክ ምርመራዎችን በማዘዝ፣** ለታካሚው ወይም ለታካሚው ቤተሰብ በራሳቸው መስራትና መጠንቀቅ የሚገባቸውን ህክምና ትምህርት መስጠት፣ ከሌሎች የህክምና ባለሙያዎች እና የህክምና ክፍሎች ጋር መመካከርና ውይይት ማድረግ፣ በተለያዩ መገናኛ ብዙኃን የበሽታ መከላከል ትምህርት መስጠት፣ የዕለት ተዕለት ኑሮ እንቅስቃሴ፣ ክህሎት ስልጠናና ህክምና ለሚያስፈልጋቸው ታካሚዎችና ለቤተ ሰባቸው የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት መስጠት፣ የተሃድሶ ህክምና ግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና በመስጠት፣ **በሙያው የዳበረ ልምድ ያላቸውን ህኪሞች በማወያየት፤ እንደአስፈላጊነቱ ለስፔሻሊስቶች በማስተላለፍ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ያለቸው የህክምና መሳሪያዎችና አዳዲስ መድሀኒቶች ወደ ተቋሙ ሲመጡ ጥቅማቸውንና ጉዳታቸውን ለማወቅ መጣር፤ ወደ ተቋም የሚመጣውን በሽተኛም ሆነ ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎችን ተከታታይ የሆነ ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ በማከናወን፣ እውቀትን ለማዳበር በየአለቱ በማንበብ እና ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም፣** መረጃዎችን በማደራጀትና የውሳኔ ሀሳብ በማቅረብ፣ **አስቀድሞ የሥልጠና ፍላጎት በመለየት፣እንዲሁም ጥናትና ምርምር በመስራት፣** ሰልጣኞቹህ ስልጠናዉን በተገቢው ሁኔታ አንዲረዱ የተለያዩ የማሰልጠኛ መንገዶቹህ በመጠቀም፣ የተሟላ መረጃ ለማግኘትናስልጠናዉ ያመጣውን ፋይዳና ፍልጎትን የሚያስችሉ ስልቶችን በመንደፍና ተግባራዊ በማድረግ **ችግሮች እንዲፈቱ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡**

3.2 ራስን ችሎ መስራት

3**.2.1** ሥራው የሚከናወንበት አግባብ

- ሥራው በሀገሪቱና በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባለዉ የሥራ ወሰን፣ የፊዚዮቴራፒ ህክምና መመሪያ እና የሙያ ስነ ምግባር በጠበቀ ሁኔታ እንዲሁም በዘርፉ የተቀመጡ ዕቅዶችን መሰረት በማድረግ ይከናወናል።

3.2.2 ***ሥራው የሚጠይቀው የክትትልና ድጋፍ ደረጃ***

- ሥራው አጠቃላይ የፊዚዮቴራፒ ህክምና ሥራው ዓላማውን ያሳከ መሆኑን እና በሌሎች የህክምና ሥራዎች ላይ ከሚኖረው ተፅዕኖ አንጻር ግምገማ ይደረግበታል።

3.3. ተጠያቂነት

3.3.1 ተጠያቂነት ለሥራ ውጤት፣

- ሥራው የታካሚዉን የህክምና ታሪክ በአግባቡ መውሰድ፣ አስፈላጊዉ አካላዊ ምርመራ ማካሄድ፣ የዲያገኖስቲክ ምርመራ ዉጤት በመመርኮዝ በሽታ መለየት፤ **ስራው አዋቂዎችንም ሆነ ህፃናትን ድንገተኛ የህክምና** እርዳታ የሚያስፈልጋቸውን ታካሚዎች ቅድመ ልይታና መረጣ (triage) ማድረግ፣ የፊዚዮቴራፒ ህክምና ያሚያስፍልጋቸው ታካሚዎች ***ታሪክ ቃለመጠይቅና የአካል ምርመራ፤ የለቦራቶሪ ምርመራዎችን፤ ለህሙማን አስፈላጊውን ህክምና መስጠትና*** ለታካሚ ግላዊ የፊዚዮቴራፒ ህክምና መስጠት፤ አስፈላጊዉን ሰው ሰራሽ አካል ፣የአካል ድጋፍና ደጋፊ የመንቀሳቀሻ መሳሪያዎች እንዲዘጋጁ በታካሚው መጠንና የድጋፍ አስፈላጊነት ልክ ማዘዝ፣ ስለ አጠቃቀማቸውም ትምህርትና ስልጠና መስጠት፤ በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰቱ የሚችሉ የእንቅስቃሴ ችግሮችንና በሽታዎችን ቀድሞ በመለየት መከላከል፣ ማከም፣ ስለ ስጋቶቹም ማስተማር ባይቻል፤ ለታካሚ የዕለት ተዕለት ኑሮ እንቅስቃሴ፣ ክህሎት ስልጠናና ህክምና ባይሰጥ፣ በተሃድሶ ህክምና ዙሪያ የሚመለከታቸዉን ማማከር ና **ጥናትና ምርምር ማድረግ፣**የሥልጠና ክፍተት መለየትና ስልጠና መስጠት፣ ሰልጣኞቸህ ስልጠናዉን በተገቢው ሁኔታ አንዲረዱ የተለያዩ የማሰልጠኛ መንገዶቸህ በመጠቀም፥ የተሟላ መረጃ ለማግኘትናስልጠናዉ ያመጣውን ፋይዳና ፍልጎትን የሚያስችሉ ስልቶችን በመንደፍና ተግባራዊ በማድረግ የሚጠይቅ ሲሆን፤
- **እነዚህ ተግባራት በሚፈለገው የጥራት ደረጃ ባይከናወኑ ወይንም ስህተቶች በወቅቱ የእርምት እርምጃ ካልተወሰደባቸው የታካሚው ህመም እየተባባሰ ይሄዳል፣ ከፍተኛ አካላዊና ስነልቦናዊ ጉዳት ብሎም ሞት ሊያስከትል ይችላል፣ በመለስተኛ ወጪ መታከም ይችል የነበረ ህመም ከፍተኛ ወጪ ወደሚጠይቁ የመድህኒትና የህክምና ደረጃዎች ሊደርስ ይችላል፣ የህክምና ጥራቱ ሊቀንስ ይችላል።። በተቋሙ የተቀመጡ ግቦችን ያስተጓጉላል አመኔታ ያሳጣል፤ የሀገሪቱ የአካል ጉዳተኛ መጠን ይጨምራል። በተቋሙ ገጽታ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል።**

3.3.2 ተጠያቂነት ለሚስጥራዊ መረጃ፣

- ***ሥራው የእያንዳንዱ ታካሚ*** የግል ጤንነት፤ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ **ሚስጥር ባይጠበቅና የታካሚ መረጃ ለማይመለከተው አካል**

ተላልፎ ቢሰጡ በታካሚው ላይ ስነልቦናዊና ማህበራዊ ጫና ያስከትላል፣ ፍተሀዊነትን ያዛበል፣ **በመሥሪያ ቤቱና በተገልጋዮች መካከል አመኔታ ማጣትና ታካሚዎች ወደ ህክምና ተቋም እንዳይሄዱ ያደርጋል።**

3.4 ፈጠራ

- ***ሥራውለእያንዳንዱ** ታካሚ ካለዉ በሽታና ችግር በተጨማሪ ሌሎች ግላዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ የፊዚዮቴራፒ ህክምና መስጠት፤ ለታካሚ የዕለት ተዕለት ኑሮ እንቅስቃሴ፣ ክህሎት ስልጠና መስጠት፣ **የተለያዩ ዘዴዎችን በመቀየስ ለህሙማንና ለቤተሰባቸው በሽታውን አስመልክቶ የጤና ትምህርትና የምክር አገልግሎት መስጠት፣ የአገሪቱን ጤና ችግር ለመቅረፍ የሚያስችሉ የተለያዩ የጤና ምርርም ላይ በመሳተፍ ምርጥ ተሞክሮችና በጥናት የተገኙ አዳዲስ አሰራሮችና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የፊዚዮቴራፒ አገልግሎቱን ማሻሻልና ዘመናዊ ማድረግ፣ የፊዚዮቴራፒና የተሃድሶ** ሕክምና የስራ፣ የትምህርትና ስልጠና መርጃዎች ማዘጋጀት፣ ትምህርትና ስልጠና መስጠት፤ ስልጠናዉ ያመጣውን ፋይዳ በጥናት መለየት፡የስልጠናዉ ፍልጎትን በጥናት መለየት **ይጠይቃል።**

3.5. የሥራ ግንኙነት

3.5.1 የግንኙነት ደረጃ

- ሥራው በውስጥ ከቅርብ ኃላፊ፣ በሥራ ክፍሉ ከሚገኙ ባለሙያዎች፣ ከሌሎች የሥራ ዘርፎች ባለሙያዎችና ኃላፊዎች፣ ከታካሚዎችና ከታካሚ ቤተ ሰቦች፣ከተለያዩ ህብረተሰቦች ክፍሎች፣ እና በአካልጉዳተኛ ዙሪያ ከሚሰሩ ድርጅቶችና ከፍተኛ ባለሙያዎች፣ ከስፖርተኞች፣ ከአሰልጣኞችና የስፖርት ዘርፍ ከሚመሩ ከፍተና አመራሮች፣ከሰልጣኞችና ከተመራማሪዎች ጋር ግንኙነት ማድረግን ይጠይቃል።

3.5.2 የግንኙነቱ ዓላማ

- **የሥራ መመሪያ ለመቀበልና ሪፖርት ለማድረግ፣ ስለሥራ ሁኔታ ለማነጋገር፣ የህክምናዉን አካሄድና ውጤትን በሚመለከት ለመወያየትና ተቀናጅቶ ለመስራት፣ በትብብር የጥናትና የምርምር ሥራዎችን ለመስራት፣ በፊዮቴራፒና ታሃድሶ ህክምና ዙሪያ ስልጠናና ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት፣ ህክምና ለመስጠት፣ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ስለ ታካሚዉ የህክምና ጉዳይ ለመወያየት፣ ስለአካል ጉዳት፣ የእንቅስቃሴ ችግሮችና በሽታዎች ስልጠና ለመስጠት፣ በአካል ጉዳተኝነት**(Disability) **ዙሪያ ለማሳከር፣ የስፖርት ላይ አደጋና ጉዳት የመከላከያ ዘዴዎችን ለማስተማር፣የስፖርተኞችን የጤና ሁኔታ ለማሳወቅና ለስፖርተኞች የጥንቃቄ እቃዎች እንዲሟሉ ምክረ ሃሳብ ለመስጠት ነው።**

3.5.3 የግንኙነቱ ድግግሞሽ

- **የግንኙነቱ ድግግሞሽ ከቀን የሥራ ሰዓት** 60% **ይሆናል።**

3.6 ኃላፊነት

3.6.1 ኃላፊነት ለሰው ሀብት

3.6.1.1 በኃላፊነት የሚመራቸው ሠራተኞች ብዛት

- የለበትም

3.6.1.2 የኃላፊነት አይነትና ደረጃ

- የለበትም

3.6.2 ኃላፊነት ለንዋይ

- የለበትም

3.6.2.1 ኃላፊነት ለንብረት

- ሥራውን ለማከናወን የሚጠቀምባቸው ኮርቸ ኮንዳክሽን ማሽን፣ ዶፕላር፣ አልትራ ሳውንድ፣ ዲያተርሚ፣ ትራንስ ኩታኒየስ ኤሌክትሪካል ኮርቸ ስቲሙሌሽን ማሽንና ሌሎች የህክምና መሳሪያዎች ግምታቸው ብር (4 ሚሊዮን) በጋራ እንዲሁም በግል የሚያዙ ዳይናሞሜትር፣ እንክሊኖሜትርና ሌሎች የህክምና መሳሪያዎችና ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ መጽሐፍ መደርደሪያ፣ ኮምፒዩተር፣ ላፕቶፕ ግምታቸው ብር 200,000.00 በአግባቡ በመያዝ የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት።

3.7. ጥረት

3.7.1 የአዕምሮ ጥረት

- ሥራዎች የታካሚዉን ታሪክ በመውሰድ፣ አስፈላጊዉን አካላዊ ምርመራ በማድረግ እንዲሁም ያዘዘዉን የዲያገኖስቲክና የላብራቶሪ ምርመራ ዉጤት በመመርኮዝ በሽታ መለየት፤ በሽታውን ከለየ በኋላ ለእያንዳንዱ ታካሚ ግላዊ (Individualized) የፊዚዮቴራፒ ህክምና መስጠት፣ መከታተል፤የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት የሚጠቅሙ ጥናትና ምርምር ማድረግ፤በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሰቱ የሚችሉ የእንቅስቃሴ ችግሮችንና በሽታዎችን ቀድሞ በመለየት መከላከል፣ ማከም፣ ስለ ስጋቶቹም ማስተማር፤ ከሌሎች የህክምና ባለሙያዎች እና የህክምና ክፍሎች ጋር ዉይይት ማድረግና ሙያዊ ውሳኔ መስጠት፤ በተሃድሶ ህክምና ዙሪያ ማማከርና አገልግሎቱን መምራት እንዲሁም ተከታታይ የሙያ ላይ ትምህርትና ስልጠና መስጠት፣ስልጠናው ያመጣውን ለውጥ መገምገምና መከታተል አስፈላጊዉን ሰው ሰራሽ አካል ፣የአካል ድጋፍና ደጋፊ የመንቀሳቀሻ መሳሪያዎች መጠንና ተስማሚነት ለይቶ ማዘዝ ስለ አጠቃቀማቸውም ትምህርትና ስልጠና መስጠት፤ ለታካሚ የዕለት ተዕለት ኑሮ እንቅስቃሴ፣ ክህሎት ስልጠናና ህክምና መስጠት የሚጠይቅ፣**ጥናትና ምርምር ማካሄድ**፣ከአቅም በላይ የሆኑ ወይንም የሌላ ባለሞያ አስተያየትና ምክር የሚፈልጉ የህክምና ችግሮችን በመለየት ወደ የሚመለከተው የህክምና ባለሙያ (ስፔሻሊስትና ሱፐር ስፔሻሊስት) ወይም ተቋም መላክ፣ **የማስተማሪያ ጽሁፎችን ማዘጋጀትና ማስተማር ሲሆን የብዙ በሽታዎች ስሜቶችና ምልክቶች ተመሳሳይነትና የሚታዘዙ የለቦራቶሪና ሌሎች ምርመራዎችን ለይቶ የማዘዝ እና በየጊዜው የሚፈበረኩ መድሀኒቶችን ጥቅምና ጉዳት ለማወቅ የሚደረግ ከፍተኛ የእውቀት ማዳበርን የሚጠይቅ ነው።፡ ከስራ ሰአቱ** 75 **ፐርሰንት ያህል ይሆናል።፡**

3.7.2.ስነልቦናዊ ጥረት

- ሥራው በህሙማን ፊት የሚነበበው ጭንቀትና ስቃይ፣ ማቃሰት የታካሚውን አስጨናቂ የሆኑ ታሪኮችን መስማት ከታካሚዎች ወይም

ከቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ከሌሎች የህክምና ተቋሙ ሰራተኞች፣ ታካሚዎችና ከታካሚ ቤተሰቦችና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር **የሚነሱ አለማግባባቶች፣ ህክምናው ረዥም ጊዜ የሚወስድ መሆኑ፣ ስሜት ፈታኝ ሲሆኑ እነዚህንም በትዕግስት ተቋቁሞ** በሥራ ላይ የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን ለመቀየርና የሚያጋጥሙ ተደጋጋሚ መሰናክሎችን በማለፍ የተሻለ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል የሥራ ትጋትንና ቁርጠኝነትን፣ ሥነልቦናዊ መሰጠትንና ዝግጅነትን ወይም ከፍተኛ ጥረትን የሚጠይቅ ነው።

3.7.3 የዕይታ ጥረት፣

- ሥራው የፊዚዮቴራፒ ህክምና መረጃን የተመረኮዘ (evidence based) መሆን ስላለበትና በየጊዜው አዳዲስ መረጃዎችን ማወቅ ስላለበት፣የህመምተኞችን የምርመራ ውጤት በኮምፒወተርና በወረቀት ላይ ማንበብና በኮምፒውተር በመታገዝ መመርመር፣ ጥናት ለማዘጋጀት፣ በየጊዜው ማንበብና እራስን ከአዳዲስ ፈጠራዎችና ግኝቶችን ጋር ማቆራኘት፣ ጥናትና ምርምር ማካሄድ ፣ ሪፖርት ለማቅረብ፣ **በኮምፒውተር በመታገዝ ማንበብና መፃፍ የሚጠይቅ ሲሆን ይህም** ከመደበኛ ስራ ሰዓቱ 50 ፐርሰንት ያህል ይሆናል።

3.7.4 የአካል ጥረት

- ሥራው 40 % በመቀመጥ፣ 10 % በእግር በመሄድ 15 % በመቆም እና 35 % ጎንበስ ቀና በማለት የሚከናወን ነው።

3.8. የሥራ ሁኔታ

3.8.1. ሥጋትና አደጋ

- በመርፌና በተለያዬ ስለታማ ነገሮች የመቆረጥና የመወጋት ለአዉራ ጣት ለወገበና ሌሎች መገጣጠሚያ ህመም የማጋለጥ ስጋት አለው።

3.8.2. የሥራ አካባቢ ሁኔታ

- ሥራው የተለያዩ የጤና ህክምና ችግሮች የተጎዱ በርካታ ህሙማን የሚታከሙበት በመሆኑ የተለያዩ በሽታ አምጪ ተዋህሲያን የተንሰራፉበትና የህሙማን ስቃይ የሚታይበት አካባቢ የሚከናወን በመሆኑ ለተለያዩ የጤና መታወክ ይዳርጋል።

3.9. እውቀትና ክህሎት፣

3.9.1. የትምህርት

የትምህርት ደረጃ	የትምህርት አይነት
የህክምና ዶክተርነት ዲግሪ	በፊዚዮቴራፒ

3.9.2 ሥራውን ለመጀመር ሚያስፈልግ የሥራ ልምድ

የሥራ ልምዱ ለማግኘት የሚጠይቀው ጊዜ	ልምዱ የሚገኝበት የሥራ ዓይነት	
6 ዓመት የሥራ ልምድ	ፊዚዮቴራፒ	
የሥራ ዝርዝሩን ያዘጋጀው ባለሙያ ሥም	ፊርማ	ቀን

የሥራ ዝርዝሩን ያጸደቀው የኃላፊው ሥም	የሥራ መደቡ መጠሪያ	ፊርማ	ቀን
